# *ከዓይን ያውጣህ*

ማን ይግጠምልህ
ማን ይዝፈንልህ
አንተ የልጅ አዋቂ
የታመቀን ፈልቃቂ
የተኛን ቀስቃሹ
የበረታን አሞጋሹ
አራስ ከአልጋ ምታስነሳ
የልብ የአንጀት ምታወሳ።

እምባዬ እያነቀኝ
እጄ ቢያሳክከኝ
ጻፊ ጻፊ እያለኝ
እሺ አልኩ
ይኸው ታዘዝኩ።

ልግጠምልህ
ልዝፈንልህ
አንበሳችን ልበልህ
የልጅ አዋቂ ነህ
አከበርኩ አደነቅኩህ
እንደ እናት ሳሳሁልህ
በሙሉ ዓይኔ ላይህ
ፈራሁ ወንድሜ
ከዓይን ያውጣህ።

ስታቀነቅን ያኔ
ከዓመታት በፊት
ነበርኩ አራስቤት
“ባይገርምሽ ገና እወድሻለሁ
ሃሳቤ ላንቺ ነው”
ያልከው
ቢመስለኝ ለልጆቼ  የዘፈንከው
ያስለቅሰኝ ነበር ያኔ
የእናት ሆዴን እያላወሰው።

አልቀረሁም መጣሁ ላይህ
6 ኪሎ ኮፊ ሃውስ
እንዳትለወጥ አደራ አልኩህ
ልጅነት ዝና  አያስትህ
ዓላማህን እንዳትረሳ
አደራ አደራ  አልኩህ
ለአደራ  እንደምትበቃ
ጨረቃዋም መስከረች
ባለሹራቡን ወጣት
በጨረቃ ብርሃን ስር መረቅኩህ።

ታዲያ ዓመታትም አልፈው
አንተም ዘፈኖችህም በስላቹ
በየሄድኩበት ሳደንቃችሁ
ተወዳቹ ተናፍቃቹ
ሲሰምር የተመረቃችሁት
ጨምሮ አየሁ ክብራቹ።

አንተ ታዲያ አዋቂው
የታመቀን ፈልቃቂው
ሃይማኖትህ ፍቅርህ
ክብርና  ቅድሚያህ
ሆና ኖሮ አገርህ
ዜማ ቅኔ ለዛ ወዝህ
ሆኖ  ኖሮ ለወገንህ
የህዝብ ልጅ የህዝብ ወዳጅ
አስታራቂ አዛማጅ።

ማን ይዝፈንልህ
ማን ይግጠምልህ
አንበሳዬ  ማን ይበልህ
ከዓይን ያውጣህ
ከዓይን ያውጣህ
ይብላኝ  እንጂ ለእናትህ
ለወለደችህ
እኔ እንኳ የሩቋ ጨነቀኝ
ፈራሁ ዓይን እንዳይበላህ።

ደግሞ  ተጽፎ አነበብኩኝ
አደራ የማትበላ
መሆንህ ተሰማና
አደራ  እንደተመረቀልህ
በወ/ሮ አበበች ጎበና።

የተሸከምከው እንዳያጎብጥህ
ህዝብ ሁሉ አደራ ሲልህ
የልቡን እየፈለቀቅክ
ትንፋሹን እየተነፈስክ
እፎይ እንድታስብለው
በዓል ሰርጉን እያደመቅክ
አበባ አየሁኝ እንድታሰኘው
ይበልጥ አደራውን ሲጥልብህ።

ቴዲያችን አንበሳችን
የሁላችንም ልጅ
የቅንነት ወንድም ወዳጅ
የልብ የአንጀት ሃኪም
አንተ የፍቅር ዶክተር
የአንድነት ማግና  ድር።

ድምጽህ ሆኖ  መሳሪያህ
ቅን ሃሳብህ እያመለጠ
ከልብህ  እየወጣብህ
የህዝብ አደራ  ሲጫንህ
እየተጨመቀ  ከውስጥ
‘ሚፈልቁት ካንደበትህ
ሞልተው ገንፍለው የፈሰሱት
ህያው ነፍስ ዘሪ ቃላቶችህ።

ለቀነኒሳ  ለሃይሌ
ለተፈሪ ለቦብ ማርሌ
ለሃይማኖት ለአብሮነት
ለሃገር ለአንድነት
ለእርቅ ለሰላማችን
ለሙዚቃ ለባህላችን
ለኢትዮጵያዊነት ክብር
ቋንቋ ከቋንቋ  እያዛመድህ
ደፈርህ ዘፈንህ
በእስራ ዓመቱ ዋዜማ
ለወገኔ በነጻ እንጂ
ለገንዘብ አልሰግድም ብለህ
ላመንክበት ደረትክን ሰጠህ።

ቴዲያችን ዳግም ልመርቅህ
ከዓይን ያውጣህ
የሃሳብህን ሁሉ ይስጥህ
እደግ አሁንም ያሳድግህ !

ፋሲካ ገ/ጻዲቅ ወ/ሰንበት
December 22, 2007
Toronto, Canada